# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ
# ADDIS NEGARI GAZETA
## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አንደኛ አመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ የካቲት ፲፪ ፪ሺ፩ ዓ.ም

First Year No.13
Addis Ababa 19th February 2009

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ


<u>ማ ው ጫ</u>


በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ማዕከላት አጠቃቀምና አስተዳደር ደንብ ........................................ገፅ ፻፳፰


CONTENT


Addis Ababa City Government Use and Administeration of Center of Micro and Small Scale Enterprises Regulation.........page 128


## ደንብ ቁጥር ፲፫/፪ሺ፩ዓ.ም

## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የማምረቻ፣ የማሳያ እና የመሸጫ ማዕከላት አጠቃቀምና አስተዳደር ደንብ

በከተማችን ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማስፋፋት ስር ሰዶ የሚገኘውን ድህነትንና ስራ አጥነትን መቅረፍ እንዲሁም የማምረቻ፣ የማሳያ እና የመሸጫ ቦታ ችግር ለመቅረፍ አስተዳደሩ ደረጃቸውን የጠበቁና ለሥራ ምቹ የሆኑ ለጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ ለቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ ለብረታ ብረትና እንጨት፣ ለምግብ ዝግጅት፣ እንዲሁም የኮንስትራክሽን ማዕከላትን በመገንባት ችግሮቹን መቅረፍ በማስፈለጉ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፳፫/፩/ረ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## REGULATION NO. 13/2009

## ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT MICRO AND SMALL SCALE ENTERPERISES MANIFACTURING DISPLAY AND SALE CENTERS USE AND ADMINISTRATION REGULATION

**WHEREAS,** It is found nessasary to abolish poverty , unemployment and reduce the problems of manufacturing, display and sale places to develop micro and small scale enterprises and build standard and well atmospheric work places and centers for textile and closing, lather and lather products, metal and wood work, food preparation, as well as constraction;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with the Addis Ababa City Government Revised charter proclamation No. 361/2003 Article 23(1) (f) the cabinet of the Addis Ababa city government has issued this regulation as follows.


ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ ‹‹የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የማምረቻና የማሳያ እና የመሸጫ ማዕከላት አጠቃቀምና አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፲፫/፪ሺ፫›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. ‹‹**ማዕከል**›› ማለት ለጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ ለቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ ለብረታ ብረትና እንጨት፣ ለምግብ ዝግጅት፣ እንዲሁም ለኮንስትራክሽን አገልግሎት በመንግስት የሚውል የተገነባ የማምረቻ ህንፃ ነው፤

፪. ‹‹**ኢንተርፕራይዝ**›› ማለት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ስትራቴጂ መሠረት በግለሰብ ወይም በቡድን አንቀሣቃሾች ባለቤትነት የተመሠረተና ካፒታሉ ከብር ፭፻ሺ /አምስት መቶ ሺህ ብር/ በታች ሆኖ ለትርፍ የተቋቋመ ተቋም ነው፤

፫. ‹‹**አንቀሣቃሽ**›› ማለት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ስትራቴጂ መሠረት ባለቤት በመሆን በማምረት ተግባር ላይ የተሰማራ ሀብት ፈጣሪና ተጠቃሚ ግለሰብ ወይም ቡድን ነው፤

፬. ‹‹**ክላስተር**›› ማለት ተመሳሳይ ሙያና የሥራ ልምድ ያላቸው ሰዎች ተያያዥ የሥራ ፍሰት ያላቸው የተለያዩ ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን በጋራ የሚያመርቱበት ቦታ ነው፤

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This regulation may be cited as the ‹‹Addis Ababa city Government Micro and Small Scale Enterprises Manufacturing Display and Sale Centers Use and Administration Regulation No. 13/2011. ››

### 2. Definitions

Unless the context requires otherwise; in this Regulation:

1. ‹‹**Center**›› means a manufacturing building built by the government for the purpose of textile and clothing, lether and lather products, metal and woodwork, food preparation and constraction services;
2. ‹‹**Enterprise**›› means an organ established by individual or group operators for profit making with less than 500,000 birr /five hundred thousand /capital based on the micro and small scale enterprise strategy;
3. ‹‹**Operator**›› means an individual or group engaged in wealth creation and use thereof in accordance with micro and small scale enterprise strategy;
4. ‹‹**Cluster**›› means a place where people who have similar profession work experience and work flow jointly manufacture market products;

፭. ‹‹**ተከራይ**›› ማለት በማምረቻ ማዕከል ለማምረት ከመንግስት ጋር የኪራይ ውል ያደረገ አንቀሣቃሽ ነው፤

፮. ‹‹**ቢሮ**›› ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ነው፤

፯.‹‹**የምርት ማሳያና መሸጫ ማዕከላት**›› ማለት አንሣቃሾች የሚያመርቷቸውን ወይም የሚሸጧቸውን አገልግሎቶች የሚያሳዩበትና የሚሸጡበት ቦታ ነው፡፡

**፫. <u>ዓላማ</u>**

ብቃት ያላቸው አንቀሣቃሾች ቅድሚያ የሚያገኙበትና ግልጽ መሥፈርቶች በመከተል የመሥሪያ ቦታ ችግራቸውን በማቃለል ምርትና ምርታማነትን ማሣደግ ነው፡፡

**፬.<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ የማምረቻ ማዕከላት ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>የማዕከላት ዓይነት፣ የኪራይ ዋጋ፣ አጠቃቀምና የእንቀሳቃሾች መምረጫ መስፈርት</u>**

**፭.<u>ዓይነት</u>**

፩. የጨርቃና ጨርቅ አልባሳት ማምረቻ፤
፪. የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ማምረቻ፤
፫. የምግብ ዝግጅት ማምረቻ፤
፬. የምርት መሸጫና ማሳያ ቦታ ፤እና
፭. የብረታ ብረትና እንጨት ማምረቻ ማዕከላት ናቸው፡፡

5. ‹‹**Rentee**›› means an operator who concluded rental contract with the government to manufacture in manufacturing centers;
6. ‹‹**Bureau**›› means the Addis Ababa City government trade and Investment Development Bureau;
7. ‹‹**Product display and sale center**›› means a place where operators display and sale their manufactured goods.

**3. <u>Objective</u>**

Increasing products and productivity by encouraging model operators and solving their problem of work place by providing clear criteria.

**4. <u>Scope of application</u>**

This Regulation shall be applicable on all manufacturing centers existing in Addis Ababa city.

**<u>PART TWO</u>**

**<u>TYPE, COST AND USE OF CENTERS AND OPERATORS SELECTION CRITERIA</u>**

**5. <u>Type</u>**

1. Textile and cloth manufacturing;
2. Lather and lather products manufacturing;
3. Food preparation manufacturing;
4. Product sale and display area, and;
5. Metal and wood work.

## ፮. <u>የኪራይ ዋጋ ዝርዝር</u>

፩. የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ማምረቻ በሜትር ካሬ ፭ ብር፤

፪. የምርት መሸጫና ማሳያ በሜትር ካሬ ብር ፲፤

፫. ለብረታ ብረትና እንጨት ማምረቻ በሜትር ካሬ ብር፪፤

፬. ለምግብ ዝግጅት ማምረቻ በሜትር ካሬ ብር ፪፤

፭. ለኮንስትራክሽን ማምረቻ በሜትር ካሬ ፶ ሳንቲም ይሆናል፡፡

## ፯. <u>አጠቃቀምና አስተዳደር</u>

፩. ማዕከላቱ የተገነቡት ሙሉ በሙል በመንግሥት በጀት ስለሆነ ባለቤቱ የከተማው አስተዳደሩ ሆኖ ማዕከላቱ በሚገኙበት ንግድና ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት ስም ይህንኑ የሚያረጋግጥ የተሟላ መረጃ ሊኖር ይገባል፡፡

፪. የማምረቻ ማዕከላቱ በሸማ ሥራ፣ በልብስ ስፌት፣ በሹራብ ሥራ፣ በጥልፍ ሥራ፣ በቆዳ ጫማና ቆዳ ውጤቶች ሥራ ለተሠማራ ብቃት ላላቸው አንቀሳቃሾች ብቻ ለ፭ ዓመት በኪራይ ይተላለፋሉ፡፡

፫. አንቀሣቃሾች ማዕከላቱ ከሚገኙበት ክፍለ ከተማ ጋር የኪራይ ውል ፈርመው የሚሠሩበትን ክፍል /የሥራ ቦታ/ ይረከባሉ፡፡ በየወሩም በካሬ ሜትር ብር ፭ ይከፈላል፣ የውሉ ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፬. በሥራቸው ብቃት ላላቸው ተወዳዳሪና ጥራት ያለው ምርት አምርተው ውጤት በማስመዝገብ ላይ ለሚገኙ አንቀሣቃሾች በተለይ ደግሞ ለሴቶች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

## 6. <u>List of Cost of Rent</u>

1. For textile and cloth manufacturing, 5(five) birr per meter square;
2. For product sale and display, 10(ten) birr per meter square;
3. For metal and wood work Manufacturing 2(two) birr per meter square;
4. For food preparation manufacturing, 2(two) birr per meter square;
5. For contraction manufacturing, 0.50 (Fifty cents) per meter square.

## 7. <u>Use and Administration</u>

1. The owner is the City Government of the center and the Trade and Industry Office should have full information in the name of which exists in the area of their existence.
2. Manufacturing centers will be rented for five years for efficient operators engaged in tailor waiving, shoes and lather products.
3. The operators will receive their working area or work place by signing lease contract with the sub city where the center exists. They will pay 5.00(five) birr per meter squar every month; content of the contract will be issued by directive.
4. Priority will be given for operators who are efficient and competitive in their work and became effective by manufacturing quality products and with special.

፭. አንቀሣቃሾች የሚመለመሉትና ተመርጠው ወደ ማምረቻ ማዕከላቱ የሚገቡት ማዕከሉ ከሚገኝበት ክፍለ ከተማ ብቻ ሣይሆን ከላይ በተቀመው መሠረት ብቃትን ማዕከል ባደረገ መሥፈርት ከሁሉም ክፍለ ከተሞች ተመርጠውና ተወዳድረው ይሆናል፡፡

፮.በማዕከላቱ ለአንቀሣቃሾች በኪራይ የሚሰጠው የቦታ ስፋት እነደየሥራ መስኩ የሚለያይ በመሆኑ በባለሙያ በጥናት በሚቀርበው መሠረት በቢሮው ይወሰናል፡፡

## ፰. <u>የአንቀሳቃሾች መምረጫ መስፈርቶች</u>

፩. ዕድሜያቸው ፲፰ ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑና የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ስለመሆናቸው የቀበሌ መታወቂያ ማቅረብ የሚችሉ፤

፪. በሽማ ሥራ፣ በልብስ ስፌት፣ በሹራብ ሥራ፣ በጥልፍ ሥራ ፣ በቆዳ ጫማና ቆዳ ውጤቶች ምርት ለማምረት ከሚመለከተው አካል ተገቢውን ፈቃድ አግኝተው ቢያንስ አንድ ዓመት በሥራ ላይ ስለመቆየታቸው ከሚሠሩበት ቀበሌ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፤

፫. አዳዲስና ቦታ ቆጣቢ ማሽኖችን በራሳቸው ገንዘብ ወይም በብድር ገዝተው ለመጠቀም ፈቃደኛ የሆኑና ይህንኑ በጽሁፍ ያረጋገጡ፤

፬. በክላስተር የተደራጁ ወይም ወደ ማዕከላቱ ከገቡ በኋላ ለሥራ አመቺ በሆነ መንገድ ለመደራጀት ፈቃደኛ የሆኑና ይህንኑ በጽሁፍ ያረጋገጡ፤

5. Operators who join the manufacturing centers shall be nominated and selected not only from their sub-city but also from all sub-cities by there effectiveness based on the criteria stated above.

6. The area of work place given to operators varies with their occupation; therefore it will be decided by the bureau after study report by experts.

## 8. <u>Operators selection criteria</u>

1. Operators who attained the age of majority and above and have Keble identity card that confirms their residency in Addis Ababa;

2. Operators who can provide evidence from their Keble that they have been engaged for one year in waiving, sewing, sweather knitting, niddling lether shoes and lather products manufacturing by aquairing proper permit from relevant organ;

3. Operators who certify by writing their willingness to buy and use new and efficient Mationaries with their own money or loan;

4. Operators associated by claster or are willing to associated in a condusive work manner after they have entered in to the center;

፭. ካፒታላቸው ከብር ፭፻ሺ (አምስት መቶ ሺህ) ያልበለጠ፤

፮. ያላቸውን የሥራ አመራርና የቴክኒክ እውቀት ለማስተላለፍ፣ ማዕከሉን በጋራ ለማስተዳደርና ለመምራት ፈቃደኛ ሆነው የገንዘብ፣ የእውቀትና የጉልበት አስተዋጽኦ ለማድረግ ዝግጁ የሆኑ፤

፯. አንቀሣቃሾቹ ሙሉ ለሙሉ ወይም በሽርክና የኢንተርፕራይዙ ባለቤት የሆኑና ይህንኑ በመረጃ የሚያረጋግጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## ክፍል ሶስት
## ስልጣንና ተግባር

### ፱. በወረዳ ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት

፩. አንቀሳቃሾችን በዚህ ደንብ መሠረት ለመመዝገብ ግልጽ ማስታወቂያ ያወጣል፤ ይመዘገባል፤ ዝርዝራቸውንም ከውሣኔ ሃሣብ ጋር ለየክፍለ ከተማው በሽኚ ደብዳቤ ይልካል፡፡

፪. ማዕከላቱ የሚገኙባቸው ወረዳዎች ለአንቀሣቃሾቹ የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በመመደብ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋ፤ ማዕከላት በውሉ መሠረት ጥቅም ላይ እየዋሉና እየተዳደሩ ስለመሆናቸው ወቅታዊ መረጃ ለክፍለ ከተማው ይልካል፡፡

6. Operators who are ready to transfer their urban management and technical skill contribute to the center by their money, knowledge and skill;

7. Operators should have to be pull or share partners of the enterprise and should certain the same with evidence.

## PART THREE
## POWER AND FUNCTION

### 9. Activities done at wereda level

1. Issue transparent advertisement to register operators based on this Regulation, and sends their list with decision proposal to all sub cities.

2. Deploy extension experts in weredas where the operators exist to moniter and give support; send recent information to the sub city regarding the services given by the centers and how to administered compliance with the contract.





5. Capitals with not more than 500.000 (five hundred thousand birr) ;

### ፲. በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ መመሪያና ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

Any law or practice inconsistent with the provisions of this Regulation shall have no effect.

## ፲፭. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ከፀደቀበት ከየካቲት ፲፪ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## 15. Effective Date

This Regulation shall enter into force as of 19th day of February, 2009.

**አዲስ አበባ**

**የካቲት ፲፪ ቀን ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም**

**ኩማ ደመቅሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**Done at Addis Ababa,**

**On this 19th Day of February 2009**

**Kuma Demeksa**

**Mayor of Addis Ababa City**



## 14. Inapplicable Laws